# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# የሕግ ፋኩልቲ

## የዲኑ የ1973 ዓ. ም. መግለጫ ።

ዳንኤል ኃይሌ ረዳት ፕሮፌሰርና የሕግ ፋኩልቲ ዲን

ዩኒበርስቲው የተቋቋመበትን ሠላሳኛውን ዓመት በዓል ያከበርንበት ያሁኑ የትምህርት ዘመን ለየት ያለ ዓመት ነበር ። ዩኒቨርስቲው የተቋቋመበትን ሠላሳኛ ውን ዓመት በማክበር ለበሳልነት ዕድሜ መድረሳችን ብቻም ሳይሆን ወደ ቀድሞ የትምህርት አሰጣጥ ዘይቤ በመመለስ የአካዳሚውን የትምህርት ደረጃ ለማሻሻል ወሳኝ እርምጃዎችን ወስደናል ። በዚህም መሠረት በሕግ ፋኩልቲ ለድግሪው ፕሮ ግራም የሚሠጠው የትምህርት ጊዜ በአንድ ዓመት እንዲራዘም ሲደረግ ይህም ብቃትና ብስለት ያላቸውን የሕግ ባለሙያዎች ለማፍራት እንደሚያስችለን እር ግጠኞች ነን ።

በዚህ አጭር ሪፖርት ውስጥ ስለፋኩልቲው መምህራንና ተማሪዎች አጠቃ ላይ ሁኔታ፣በምርምር ሥራዎችና የሥርዓተ ትምህርት ጥናት በኩል ስላለው እንቅ ስቃሴና፣የቀድሞ የሕግ ተማሪዎችን ማህበር ለማቋቋም ስለተደረገው ጥረት አጠር ያለ መግለጫ ሲሰጥ በመጨረሻም ጐላ ብለው የሚታዩ አንዳንድ ፍላጐቶችንና እክሎችን ለመጠቆም ተሞክሯል ።

## 1. ተማሪዎች

በ1973 ዓ. ም. የትምህርት ዘመን መጀመሪያ ላይ ለዲግሪው ፕሮግራም የተ ቀበልናቸው መደበኛ ተማሪዎች ቁጥር 214 ሲደርስ በማታው የትምህርት ክፍል ለዲፕሎማ ፕሮግራም የተመዘገቡት 176 ተማሪዎች ነበሩ ።

የተማሪዎቹ ዝርዝር በዓመታቸውና በአካዳሚክ አቋማቸው መሠረት ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ እንደተመለከተው ነው ።

### በ1973 ዓ. ም. የትምህርት ዘመን ለኤል ኤል ቢ ዲግሪ ፕሮግራም በሕግ ፋኩልቲ የተመዘገቡ ተማሪዎች ብዛት

#### አንደኛ ሴሚስተር ።

| | ጠቅላላ ተመዝጋቢ | በማስጠን ቀቂያ ላይ የነበሩ | በመጨረሻ ማስጠንቀ ቂያ ላይ የነበሩ | የወደቁ | አስፈላጊ ውን ፎርማ ሊቲ ሳያሟ ሉ የቀሩ | በልዩ ልዩ ምክንያት የለቀቁ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1ኛ ዓመት ሕግ | 78 | 7 | 7 | — | 2 | 3 |
| 2ኛ ዓመት ሕግ | 84 | 24 | 4 | 4 | 3 | 1 |
| 3ኛ ዓመት ሕግ | 43 | 14 | 1 | — | — | — |
| 4ኛ ዓመት ሕግ | 9 | — | — | — | — | — |
| | 214 | 45 | 12 | 4 | 5 | 4 |

ሁለተኛ ሴሚስተር ።

| ሕግ ት/ቤት | ጠቅላላ ተመዝጋቢ | በማስጠን ቂያ ላይ የነበሩ | በመጨረሻ ማስጠንቀ ቂያ ላይ የነበሩ | የወደቁ | አስፈላጊ ፎርማሊቲ ሳያሟሉ የቀሩ | በልዩ ልዩ ምክንያት የለቀቁ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1ኛ ዓመት | 73 | 2 | 5 | 2 | 3 | — |
| 2ኛ ዓመት | 84 | 8 | 9 | 4 | 1 | 2 |
| 3ኛ ዓመት | 45 | — | 1 | — | — | — |
| 4ኛ ዓመት | 8 | — | — | — | 1 | 1 |
| | 210 | 10 | 15 | 6 | 3 | 3 |

*የማታው ዲፕሎማ ፕሮግራም ፤*

በ1973 የትምህርት ዘመን የዲፕሎማ ፕሮግራም በተሟላ ሁኔታ ሲካሄድ የቆየ ሲሆን በመጀመሪያው ሴሚስተር 101 የ1ኛ ዓመት ፣ በሁለተኛ ሴሚስተር 75 የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች ነበሩ ።

በዓመቱ መጨረሻ 7 ተማሪዎች በድግሪ ፣ 61 ደግሞ በዲፕሎም ተመርቀዋል።

በአንደኛው ሴሚስተር ያብዛኞቹ ተማሪዎች ውጤት አጥጋቢ ስላልነበረ ይህንኑ ለማሻሻል ሲባል በትምህርትታቸው ደከም ብለው የተገኙትን ተማ ሪዎች ከፋካልቲው መምህራን አማካሪዎች እንዲመደብላቸው ተደረገ ። በዚህ መሠረት እያንዳንዱ መምህር ከሶስት እስከ አራት የሚደርሱ ተማሪዎችን በቅርብ ሆኖ የማማከሩን ሥራ ይዞ በመጨረሻው ዓመት የተማሪዎቹ ውጤት ማሻሻል የዚህን ዕቅድ መሳካት የሚያሳይ ነው ብለን እናምናለን ።

የተማሪዎችን የትምህርት ይዞታ ለማሻሻል ሌላው የተወሰደው እርምጃ ቀ ደም ብሎ ሲደረግ እንደነበረው የክረምት የጥናት ፕሮግራም በማዘጋጀት አንብ በው መጥተው ዩኒበርስቲው ሲከፈት ለፈተና እንዲቀመጡ ማድረግ ነበር ።

በመጨረሻም በውጤቱ ብልጫ ለሚያሳይ ተማሪ በየዓመቱ ሽልማት ለመ ስጠት የሚያስችል በፕሮፌሰር ጆርጅ ኪችኖብች ስም የሚጠራ የሽልማት እቅድ የገንዘብ ምንጭ ለመፍጠር ታስቧል ። ይህ ውጥን ገና ፍጻሜ ያላገኘ ቢሆንም የአ ካዳሚውን የትምህርት ይዞታ የላቀ ለማድረግ ጥሩ ማበረታቻ ይሆናል ብለን እና ስባለን ።

2. *መምህራን*

*ሀ/ የድግሪ ፕሮግራም ፤*

በዚህ ዓመት ካሉን አሥራ አራት መምህራን አሥራ አንዱ ኢትዮጵያውያን ሲሆኑ ሶስቱ የውጪ አገር ዜጎች ነበሩ ። ከነዚህ በዓመቱ መጨረሻ ፕሮፌሰር ጆርጅ ክችኖቢች የፋካልቲው የ29 ዓመት ከፍተኛ አገልግሎት ካበረከቱ በኋላ ጡረታ ወጥተዋል ።

በዓመቱ መጨረሻ ሁለት የውጪ ዜጎች ማለትም ዶክተር ሄንሪክ ሌስቹናና ዝጅስዋብ ጋሊትስኪ የኮንትራት ጊዜያቸውን ጨርሰዋል ። እኚሁ ከፖላንድ ዋርሶ ዩኒቨርስቲ የተላኩልን መምህራን በፋካልቲያችን በቆዩበት ሶስት ዓመታት ከፍ

ተኛ ተሳትፎ አሳይተዋል ። በዚህም ረገድ በፋካልቲያችንና በዋርሶ ዩኒቨርስቲ መካከል የተፈጠረው ጥሩ አርአያነት ያለው ግንኙነት የበለጠ እንደሚጠናከር እርግጠኞች ነን ።

በተጨማሪም ያሉንን መምህራን ዕውቀት ለማዳበር ባለን ዕቅድ መሠረት ዘንድሮ ሁለት መምህራን ማለትም አቶ በላይነህ ስዩም ወደ ካናዳ ማክጊል ዩኒቨ ርስቲ ፥ አቶ ሰለሞን ጅሩ ዩናይትድ እስቴት ኦፍ አሜሪካ በሚገኘው ኮለምቢያ ዩኒበርስቲ ትምህርታቸውን ለመከታተል ተልከዋል ።

ከላይ የተጠቀሱትን ብቁ መምህራን የመተካቱ ተግባር ዘግየት ብሎ የተጀ ሙረ ሲሆን በተረገው ያላሰለሰ ጥረት ሌሎች ጥልቅ ዕውቀት ያላቸውን ምሁራንን ለማግኘት በመቻላችን ጥረታችን አኩሪ ውጤት ማሳየቱን ልገልጽ እወዳለሁ ። ስለሆነም በመጪው የትምህርት ዘመን መጀመሪያ ላይ ዶክተር ሚካኤል ሄርማን ከፖላንድ ሕዝባዊት ሪፑብሊክ ፥ ዶክተር ሐርስት ክልነር ከጀርመን ዲሞክራትክ ሪፓብሊክ ፥ አቶ መስፍን ገ/ሕይወትና አቶ ዘካርያስ ቀንዓ በፋካልቲያችን ለማስ ተማር ይመጣሉ ።

እንደተለመደው የፋካልቲው መምህራን ትምህርት በሚነኩና ከዚያም ውጪ አስተዳደርን በሚመለከቱ ብዙ ጠቃሚ ጉዳዮች ተካፋዮች ነበሩ ። ይህም እያንዳ ንዱ አስተማሪ የሚያበረክተው ብቻ ሳይሆን የሕግ ትምህርት ቤት የሚሳተፍባቸ ውን ተግባሮች ስፋት ያሳያል ። በተቻለ መጠን እያንዳንዱ መምህር በተለይ ጥናት የሚያደርግበትን አካባቢ በቅርብ እንዲከታተል ለማድረግና በየወቅቱ በሚፈጠ ሩት አዳዲስ ሁኔታዎች ላይ ለመወያየት እንዲያስችለን የፋካልቲ ሴሚናር የተሰኘ መድረክ ከፍተናል ። ምንም እንኳን በዚህ ዓመት የተካሄዱት ሴሚናሮች የመጨ ረሻ ዓመት ተማሪዎችንና መምህራንን ብቻ የሚያቅፍ ቢሆንም ለወደፊቱ ተስፋፍ ተው በሰሚናሩ ለመሳተፍ ፍላጐታቸውን የገለጹልንን የቀድሞ ተማሪዎች ለመ ጨመር እንደሚበቃ ተስፋ አለን ። ባለፈውም የትምህርት ዘመን በሚከተሉት ርዕሶች ላይ ሴሚናሮችና ተከታታይ ንግግሮች ተደርገዋል ።

1. « የሶሻሊስት ዲሞክራሲ መስፋፋት ችግሮች » በዶክተር አለክሳንደር ፓፓቭ ከሞስኮ ዩኒቨርስቲ
2. « ከማርክሳዊ የመንግሥት ቲዎሪ ውስጥ የእኩልነት ጽንሰ ሃሳብ በዶክተር ሄንሪክ ሌስቼና (ከሕግ ፋካልቲ)
3. ስለ ዘመናዊ መንግሥት ሕጋዊነት በአፍሪካ » ፤ በዶክተር ሄንሪክ ሾለር (ከሙኒክ ዩኒበርስቲ)
4. « ከፋብሪካ በሰው የሚመረቱ ዕቃዎች የሚያስከትሉት ሃላፊነት » በፕሮፌ ሰር ጃርጅ ቺችኖብች ።

ለ/ የማታው ዲፕሎማ ፕሮግራም ፤

የሕግን ተከታታይ የትምህርት ፕሮግራም ከመደበኛው የትምህርት ክፍል ጋር በተቻለ መጠን ለማዋሐድ የፋካልቲው የምን ጊዜም ፖሊሲ እንደሙሆኑ መጠን ይህንንም ለማድረግ በተቻለበት አንደኛው መንገድ የሙሉ ጊዜ መደበኛ መምህራን በማታውም የማስተማር ፕሮግራም ለመሳተፍ እንዲችሉ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ነው ። ስለሆነም በአንደኛውና በሁለተኛው ሴሚስተር ሲያስተምሩ ከነበሩት አሥራ አራት መምህራን መካከል ከሕግ ፋካልቲ ውጪ ያመጣናቸው ሁለት ብቻ ነበሩ ። ጥሩ ውጤት ለማስገኘት እንዲቻል መምህራኑ በማታውም ፕሮ

ግራም መደበኛ ተማሪዎችን የሚያስተምሩት የትምህርት ዓይነት እንዲይዙ ሲደረግ በዩኒቨርስቲው ደንብ መሠረት ከአንድ የትምህርት ዓይነት በላይእንዳያስተምሩ የተደረጉ አስተማሪዎችም አልነበሩም ።

### 3. የሥርዓተ ትምህርት ጥናትና ግምገማ ፡፡

የሥርዓተ ትምህርት ጥናትና ግምገማ የዘወትር ሂደት እንደመሆኑ መጠን ፋካልቲው ባጠቃላይም ሆነ የትምህርት ደረጃዎች ዕድገትና የሥርዓት ትምህርት ኰሚቴው በተለይ የሚያስቡበት ጉዳይ ነው ። ምንም እንኳን የኰሚቴው አብይ ተግባር የሆነው አዲሱ የአምስት ዓመት የኤል ኤል ቢ ዲግሪ ከሥርዓተ ትምህርት ተዘጋጅቶ የመቅረብ ሥራ በ1972 የትምህርት ዘመን የተጠናቀቀ ቢሆንም ተደቅኖ የነበረው ይህንን ፕሮግራም ትምህርታቸውን በደሮው ፕሮግራም የጀመሩት ነገር ግን ትምህርታቸውን ያላገባደዱት ተማሪዎች ሥራ ላይ ማዋሉ ነበር ። የሕግ ሶስተኛ ዓመት ማለትም የዩኒቨርስቲ አራተኛ ዓመቴ ተማሪዎች ምረቃ በ1973 ዓ. ም. የትምህርት ዘመን መጀመሪያ ሴሚስተር ፍጻሜ ላይ እንዲሆን ኮሚቴው ያቀረበው ሃሳብ ለፋካልቲው የአካዳሚክ ጉባኤና ለዩኒበርስቲው የሥርዓተ ትምህርትና የደረጃዎች ግምገማ ኮሚቴ ቀርቦ ጸድቋል ።

የአምስት ዓመቱን የኤል ኤል. ቢ. ዲግሪ ፕሮግራም ተግባራዊ ከማድረጉም በተጨማሪ ኰሚቴው የአካዳሚክ ጥራትን ጉዳይ በሚገባ አጢኖታል ። በዚህም ረገድ ፤

- ሀ/ የ፡ረምት ምንባቦች እንዲዘጋጁ
- ለ/ ተማሪዎች በአነስተኛ ክፍሎች እንዲከፋፈሉ
- ሐ/ ለተግባራዊ ትምህርት ትኩረት እንዲሰጥ
- መ/ የትምህርት ዓይነት መደበኛ ይዘት እንዲኖረው ሀሳብ አቅርቧል ።

ባለፈው የትምህርት ዓመት መጨረሻ ላይ የቀረቡትም ሐሳቦች በመጪው የትምህርት ዓመት ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ ይውላሉ ። ኮሚቴው የተወያየበት ሌላው ጉዳይ ደግሞ የፋካልቲው አካዳሚክ ጉባኤ ፈተናዎችን የሚቆጣጠርበት ሁኔታ ነው ። እስካሁንም ቢሆን ፈተናዎች ከመሰጠታቸው በፊት አስቀድሞ በአካዳሚክ ኮሚሽን ሲታይ የነበረ ቢሆንም የኰሚሽኑን ሥልጣንና የመምህሩን ነጻነት ማገናዘብ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል ። ይህንን በሚመለከት ኰሚቴው ያቀረበው ሀሳብ ገና በአካዳሚክ ጉባኤው ይጠናል ።

### 4. ምርምርና የኅትመት ሥራዎች ፤

የምርምርና የጽሑፍ ሥራዎች እንደገና በማንሰራራት ላይ ቢገኙም ባለብን የመምህራን እጥረት የተነሳ ዕቅድ ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ አልዋለም ። ቢሆንም በቂ መምህራን ለማግኘት ባለን ተስፋ መሠረት ሥራውን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማካሄደ በሚያስችሉን ጉዳዮች ላይ ተነጋግረናል ።

### ሀ. በመካሄድ ላይ ያሉ የምርምር ጥናቶች ዕቅድ ፤

### 1. የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት

እንጋፋ የሆነው ይህ መጽሔት ለጥቂት ጊዜ መታተሙ ሲቋረጥ ከሁለት ዓመት ወዲህ ቀጥሎ ቅጽ 11 ቁጥር 1 በዚህ ዓመት ታተመ ። ተከታዩን ቅጽ 11 ቁጥር 2 ለማውጣት ሥራው የተገባደደ ስለሆነ በመጪው የትምህርት ዘመን በመጀመሪያዎቹ ሶስት ወራት ገደማ ይታተማል ተብሎ ይጠበቃል ።

## 2. የተጠቃለሉ የኢትዮጵያ ሕጎች ፤

የዚህ ዕቅድ ሥራ ባለፈው የትምህርት ዘመን ተጀምሮ አሁን ሁለተኛውን ክፍል በማዘጋጀት ላይ ስለለን ሁለተኛው ክፍል በሐምሌ ወር በ1974 ይጠናቀቃል ተብሎ ይጠበቃል ።

## 3. የአፍሪካ ሕግ ዳይጀስት ፤

ይህ መጽሔት ከ1966 ወዲህ ኅትመቱ ተቋርጧል ። ፋካልቲው መጽሔቱን መታተም እንደገና ለመቀጠል በየጊዜው ባደረጋቸው ስብሰባዎች የተነጋገረበት ቢሆንም በገጠመን የልዩ ልዩ ቋንቋ አዋቂዎች እጥረት ምክንያት እስካሁን ድረስ ሳይሳካ ቆይቷል ። ይህንንና የመሳሰሉት ችግሮች በመጪው ዓመት መጀመሪያ አጋማሽ ላይ እንደምንወጣውና ኅትመቱ እንደሚቀጥል ተስፋ አለን ።

### ለ/ የግል ምርምር ጥናት ፤

ከላይ ከተጠቀሱት በፋካልቲው በመካሄድ ላይ ከሚገኙት የምርምር ጥናቶች ሌላ መምህራን በየግላቸው ያደረጉት ጥናት ለማስተማሪያ የሚሆኑ ማቴሪያሎች ንና በመጽሔት የሚታተሙ አጫጭር ጹሑፎችን በማዘጋጀት በኩል ረድቷል ። ከነዚህም ሳይጠቀስ የማይታለፍ ስለ ውል አመሠራረት በፕሮፌሰር ጆርጅ ቺቸኖ ብች የተዘጋጀው ጽሑፍ ነው ። እኚህ ፕሮፌሰር በውል አመሠራረት ላይ ያዘጋጁ ትን ትችት ረቂቅ አጠናቅቀው በዓመቱ መባቻ ገደማ ለፋካልቲው አቅረበዋል ። ሥራቸውም በውስጥና በውጭ ገምጋሚዎች ታይቶ ለኅትመት ብቁ መሆኑ የታመ ነበት ሲሆን የገምጋሚዎቹ አስተያየት ታክሎበት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለዩኒቨርስቲው የምርምርና የኅትመት ክፍል ቀርቧል ።

የምርምርና የኅትመት ጥረታችን በሽያጭ አንጻር የታየ እንደሆነ የሚያመረ ቃ ሊሆን አልቻለም ። እስካሁን እትሞቻችን ገበያ የሚቀርቡት አራት ኪሎ ግቢ በሚገኘው የዩኒቨርሲቲ መጻሕፍት መሸጫ ብቻ ነው ። ለሌሎች የመጻሕፍት መሸ ጫ መደብሮች ከሚሸን ተከፍሎ እትምታችን ለሕዝብ የሚቀርቡበት ሌላ ዘዴ ካልተገኘ ሥራችን ተስፋ ቢስ ሆኖ ይቀራል ። እትምታችን ሕዝቡ እንዲያገኛቸው ካልተደረገ የምናካሂደው ሥራ እንኳን ፍሪያማ ሊሆንና መቀጠሉም አጠራጣሪ ነው ። በዚህ አንጻር እስካሁን ችግሮች የገጠሙን ቢሆንም የሥራችን ውጤት ጠ ቀም ያለ እንዲሆን ማረጋገጥ ብቻም ሳይሆን በሕግ ሙያ የተሰማሩትን ሰዎች በማ ስተማር አቢይ ዓላማችንን እግቡ ለማድረስ የሚያስችል አሠራር መቀየስ ይኖር በታል ።

## 5. ቤተ መጻሕፍትና መረጃዎች ፤

ባያዝነው ዓመት የቤተ መጻሕፍታችን ይዘት ጉልህ የሆነ መሻሻል አሳይቷል። ከጀርመን ፌደራል ሪፑሊክ መንግሥትና ከዓለም አቀፍ የቀይ መስቀል ማህበር በስጦታ ያገኘናቸው በዛ ያሉ መጻሕፍት የመጻሕፍታችንን ብዛት ከፍ አድርገው ታል ። ከዚህ የሚከተለው ዝርዝር እ. ኤ. አ. ከነሐሴ 1 ቀን 1980 እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1981 ዓ. ም. መጻሕፍት ቤቱ ያሳየውን ዕድገት ያመለክታል ።

| | |
|---|---|
| አዲስ ጭማሪ በርዕስ | 130 |
| በስጦታ የተገኙ ማቴሪያሎች በጥቅል | 170 |

በደምበኝነት የተገኙ ወቅታዊ እትሞች በርዕስ ——————76
በልውውጥ የተገኙ ወቅታዊ እትሞች በርዕስ ——————25
በስጦታ የተገኙ ወቅታዊ እትሞች በርዕስ ——————20

በአገልግሎት በኩል ተጠቃሚው በብዛት ከመጨመሩም በላይ የአዘውታሪውም ቁጥር ፈጣን ዕድገት አሳይቷል ። ቤተ መጻሕፍቱ ለ390 ተማሪዎች ፣ ለ16 መምህራንና በቴክኒክና በአስተዳደር ሥራዎች ለተሰማሩ 21 ሠራተኞች አገልግሎት በመስጠት ላይ ነው ። ከዚህም በላይ ለዩኒቨርስቲው የሌሎች ክፍሎች ተማሪዎችን መምህራንና በሌላም ሙያ የተሰማሩ ግለሰቦችን ያገለግላል ።

## 6. የቀድሞ ተማሪዎች ፤

ባለፉት ጊዜያት የቀድሞ የሕግ ተማሪዎችን ማህበር ለመመሥረት ጥረት የተደረገ ቢሆንም በያዝነው ዓመት ከተወሰዱት ትላልቅ እርምጃዎች መካከል ለሕግ ፋካልቲ የቀድሞ ተማሪዎች ማህበር መቋቋም መሠረት መጣሉ ነው ። የማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ ረቂቅ አቶ ኃይሌ ከበደ (ጠበቃ) አቶ ግርማ አስፋው (ከሕግና ፍትሕ ሚኒስቴር የሕግ ክፍል) ፤ አቶ መክብብ ጸጋው (የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ) አቶ ዮሴፍ ገ/እግዚአብሔር (በሕግ ፋካልቲ ረዳት ፕሮፌሰር) እና አቶ ዘርዓ ብሩክ አበራ በኢች ቢ. ኤ. ዋና የሕግ አማካሪ በአባልነት በሚገኙበት አርቃቂ ኮሚቴ ተዘጋጅቷል ።

የተዘጋጀውም የመተዳደሪያ ደንብ ረቂቅ የየክፍሉ ተወካዮች በሚገኙበት አስተባባሪ ኮሚቴ ከተጠና በኋላ የማህበሩን መመሥረት የሚያረጋግጥ ሰነድ እንደገና በመዘጋጀት ላይ ነው ። ማህበሩም ከመጪው የትምህርት ዓመት ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል የሚል ተስፋ አለን ።

## 7. የሚያስፈልጉ ነገሮችና ያሉት ችግሮች

በቂ የሆነ ሕንጻ አለመኖር በተማሪዎችና በሚያደርገው እንቅስቃሴ አንጻር የሕግ ፋካልቲ በከፍተኛ ፍጥነት እየተስፋፋ የሚሄድ ቢሆንም ቀድሞ በተመሠረተበት ቅጽር ተወስኖ ይገኛል ። ዋናው ሕንጻና ሌሎችም በዙሪያው ተበታትነው የሚገኙት ለተግባሩ ብቁ አለመሆናቸውም ብቻ ሳይሆን በእርጅና ወይም በጥገና እጦት የተነሣ ወይም በሁለቱም ምክንያት በውስጣቸው ለሚካሄደው ሥራ ሥጋት እየተፈጠሩ ነው ። በእኔ አስተያየት ለፋካልቲው መንቀሳቀሻ የሚበጅ ብቃት ያለው የሕንጻ ሥራ የሚታሰብበት ጊዜ አሁን መሆን አለበት ።

### የውጭ ግንኙነቶች ፤

የፋካልቲው ዕድገትና ታዋቂነት የሀሳቦች ልውውጥና ከብዙ የውጭ ተቋሞች በሚያደርግለት ትልቅ የገንዘብ ዕርዳታ ውጤት ነው ። የቀድሞ ግንኙነቶቻችን ጨርሰው የተቋረጡ ሲሆን ከሌሎች ተቋሞች ጋር አዲስ ግንኙነት ለመፍጠር የተወሰደ እርምጃ እምብዛም ነው ። እያንዳንዱ ፋካልቲ በአንጻሩ የሚያደርገው ጥረት የማይናቅ ቢሆንም ቅሉ ማዕከላዊነት ያለው ዩኒቨርስቲ አቀፍ የሆነ አሠራር የበለጠ ፍሬያማ ስለሚሆን ለችግሩ በዚህ አንጻር መፍትሔ ቢፈለግለት ጠቃሚ ነው ።

## መደምደሚያ ፤

የገጠሙን ችግሮች ታዳጊ ተቋሞችን ከሚገጥማቸው የተለየ አይደለምና ያለንን አጥብቀን እንደያዝን በአስተሳሰብ ወደ ፊት መራመድ አለብን የፋካልቲያችን የቀድሞ ዲን አንድ ጊዜ እንዳወሱት አንድ ነገር ባለበት እንዲንቀሳቀስ ከማድረግ ይልቅ ካለበት ማንቀሳቀሱ የበለጠ ከባድ መሆኑን የሳይንስ ሕጐች ያስተምሩናል ። ሰብአዊ ተቋሞች ግን ሁላችንም እንደምናውቀው ሌላ ሕግ አላቸው፣ አንድን ተቋም ወይም ፕሮጀክት መጀመሩ ሳሆይን ማካሄድ ወይም አሳክቶ ከፍጻሜ ማድረሱ የበለጠ አድካሚ ነው ። ሆኖም ግን በፋካልቲው የሥራ ባልደረቹና በተማዎቻችን የኅብረት መንፈስ እርምጃችን እንዲቀጥል ማድረግ ብቻም ሳይሆን ፋኩልቲው በትክክለኛ አመለካከት የታነጸና በአርአያነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ባለሙያዎችን በማፍራት የሚጠበቅበትን ለማሟላት እንደሚችል ቅንጣት ያህል አልጠራጠርም ።